ክፍል 3 ፓለቲካዊ መብቶችን ማክበር፤ የዜጎች መንግሥታቸውን የመለወጥ መብት፤

ሕገ መንግስቱና ሕጉ ዜጎች መንግሥታቸውን በሰላማዊ መንገድ የመለወጥ መብት እንዳላቸው እና ይህንኑ መብታቸውን በተግባር ነፃና አድሎ የሌለበት ምርጫ በማድረግ ይጠቀሙበታል ይላል፡፡ ይሁን እንጂ የተከሰቱ ስህተቶችና መራጮችንና የምርጫ ታዛቢዎችን ማስፈራራት የ2005ቱን ምርጫ ሂደት በብዙ ቦታዎች ያበላሹ ተግባሮች ነበሩ ገዥው ፓርቲ የኢህአዴግ ገዢ በመንግስቱ አሠራር ላይ የበላይነት በመንግሥ ነበረው፡፡

መንግሥት በብሔር ብሔረሰቦች ፌዴሬሽን ላይ የነበረው ፖሊሲ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሁሉም ዋና ዋና ብሔር ብሔረሰቦች እንዲወከሉ አስችሏቸዋል፡፡ ይሁን እና የአናሳ ብሄረሰብ ቡድኖች በሕግ አውጭው አካል ውስጥ ውክልና አላገኙም፡፡ በስድስት ክልላዊ መንግሥታት 23 ብሔረሰቦች በፓርላማው ውስጥ ወንበር ለማግኘት የሚያበቃ የሕዝብ ቁጥር አልነበራቸውም፡፡ ይሁን እንጂ በግንቦት 2005ቱ ምርጫ ከነዚህ ብሔሮች የተውጣጡ ግለሰቦች 547 መቀመጫዎች ባሉት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ ላሉ 23 ልዩ መቀመጫዎች ተወዳድረው ነበር፡፡

ምርጫና የፖለቲካ ተሳትፎ

እንደ ሃገር ውስጥና የውጪ ታዛቢዎች ኢህአዴግ ከ547ቱ መቀመጫዎች 372ቱን ያሸነፈበት የግንቦት 2005ቱ ብሔራዊ ምርጫ ባጠቃላይ የሕዝቡን ፍላጎት ያሳየ ነበር፡፡ ተቃዋሚ ፓርቲዎችም ያልተጠበቀ ጥንካሬ ያሳዩበትና በፓርላማ ያሉ ተወካዮቻቸው ቁጥር ከ12 ወደ 172 ያደገበት ነበር ፡፡

መራጮችን እና የምርጫ ታዛቢዎችን ማስፈራራትን ጨምሮ የተለያዩ ስህተቶች በብዙ ቦታዎች ላይ የምርጫውን ሂደት አበላሽተውት ነበር ፡፡ መንግስትና ኢህአዴግም የ"መጨረሻ" ያሉትን የምርጫ ውጤት ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ከመግለፁ በፊት ገልፀው ነበር ፡፡ በተለይም በአማራ፤ኦሮሚያ እና በደቡብ ብሔር ብሔረሰብና ሕዝቦች ክልሎች ውስጥ ግድያዎች፤ መሰወሮች፤ የመራጭ ማስፈራራትና ማዋከብ እንዲሁም ሕገ ወጥ እስሮች በተቃዋሚ ፓርቲ ደጋፊዎች ላይ መድረሱን ታዛቢዎች ሪፖርት አድርገው ነበር ፡፡ (ክፍል 1 ሀን፤ለንና መን ይመለከቱ) የካርተር ማዕከል የታዛቢዎቹ ቡድን "የምርጫ ሳጥኖች ያለአግባብ መዘዋወር እንደነበረ፤ በስርዓቱ የተቆለፉ እንዳልነበረ ወይም የፓርቲ ሰዎች ከምርጫ ጣቢያዎች መታገድ እንደነበረ ወይም ሙሉውን የቆጠራ ሁኔታ እንዳይከታተሉ እንደተደረገ ማስረጃ አግኝቷል "በማለት ያለውን ስጋት ገልጿል ፡፡ በተጨማሪም " በምርጫው ዕለትና ከምርጫው በኋላ ማስፈራራትና ማዋከብ " እንደነበር ሪፖርት አድርጓል፡፡ የአውሮፓ ሕብረት የምርጫ ታዛቢዎች ልዑክ ሃላፊ ቅድመ ሪፖርት ባንዳንድ ቁልፍ ቦታዎች የተከሰቱ ችግሮችን በመጥቀስ እንደሚያመለክተው ከምርጫው በኋላ የነበረው ቅሬታ የማጣራት ሂደት " የአለም ዓቀፍ ደረጃን ያልጠበቀ ነበር " ብሏል ፡፡ እነዚህ ሁሉ ትችቶች ቢኖሩም ግን አለምዓቀፍ ታዛቢዎች ምርጫው አገሪቱ በምታደርገው የዴሞክራሲ ጉዞ ትልቅ እርምጃ እንደነበር ይናገራሉ ፡፡

ምርጫውን ተከትሎ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የገዢው ፓርቲ መሣሪያ እንደሆነና በምርጫ ስላጋጠሙና በገዢው ፓርቲ ደጋፊዎች ስለተደረጉ የምርጫ ኮሮጆን የመሙላት፤የቆጠራ ማጭበርበር፤ጉቦ፤ግድያዎች ፤ደብዳባዎችና ሰፊ የማስፈራራትና የማዋከብ ተግባራት ሲነገረው ምንም እርምጃ ባለመውሰዱ ከሰውታል፡፡

በሰኔ 2005 በገዢው ፓርቲና በዋናዎቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል በምርጫ ቅሬታዎች ላይ በተደረገው ድርድር ብዛት ያላቸውን የምርጫ ቅሬታዎች የሚፈታ አንድ ጊዜያዊ ሂደት እንዲፈጠር ስምምነት ላይ ተደርሶ ነበር ፡፡ እንደ ካርተር ማዕከል መግለጫ 44 የተለያዩ አጣሪ ኮሚቴዎች ባገሪቱ በ178 የምርጫ ጣቢያዎች የነበሩ

ቅሬታዎችን አጣርተውና ተመልክተው ነበር ። የነዚህ ኮሚቴዎች ግኝትም የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በ31 ምርጫ ጣቢያዎች ድጋሚ ምርጫ እንዲያካሂድ ምክንያት ነበር ። በነዚህ የምርጫ ጣቢያዎች አዲሱ ምርጫ ተካሂዶ የነበረው በነሐሴ 2005 ነበር ።

በመስከረምና ጥቅምት 2005 መንግሥትና የተቃዋሚ መሪዎች ተቃዋሚዎች በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ ስለሚኖራቸው ተሳትፎ ተወያይተው ነበር ። አብዛኛው የሕብረት አባላት ፓርላማ ለመግባት ሲሰማሙ አንዳንድ የቅንጅት አመራሮች በፌደራል ፓርላማ ውስጥ ሆነ በክልል ፓርላማዎች እንዲሁም በአዲስ አበባ ፓርላማ እንደማይገቡ አስታውቁ ። ይሁን እንጂ ባመቱ መጨረሻ አብዛኛው የቅንጅት አባላት ፓርላማ ገብተው ነበር ። በጥቅምት መጨረሻ ቅንጅት ሕዝቡን ለሰላማዊ ተቃውሞ ጠርቶ ነበር ። በዚህ ተቃውሞ ሕዝቡ ጡሩንባ እንዲያሰማ፤ በኢህአዴግ ባለቤትነት ከሚተዳዳሩ ንግዶች እንዳይገበያይ፤ እንዲሁም የመንግሥት ደጋፊዎችን ማግለል የመሣሠሉትን መንግሥት በግልፅ ሕገወጥ ያላቸውን ተግባራት እንዲያደርግ ቀስቅሰው ነበር ።

ከህዳር 1 ፤2005 ጀምሮ በተቃዋሚዎች ተደራጁ የተባሉ ፀረ-መንግሥት አመፆች አዲስ አበባ ውስጥ በመከሰታቸዉ መንግሥት በዛ ያሉ የተቃዋሚ አመራሮች እንዲሁም የነፃ ጋዜጣውን እና የሲቪል ማሕበረሰቡን አባላት በሕገ ወጥ ተግባራት ተሳትፈዋል በሚል በቁጥጥር ሥር አውሏቸው ነበር ። የፀጥታ ሃይሎች ከ30,000 እስከ 50,000 የሚደርሱ ተቃዋሚዎችን ያለ ክስ አስረው ነበር ።

የጦር ሰራዊቱ ጣልቃ ገብነትም በማንአለብኝነት ግድያዎችንና እስር የመሳሰሉ ሰፋ ያሉ የመብት ጥሰቶችን አስከትሎ ነበር ። የፀጥታ ሃይሎች ከ20ው የቅንጅት ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ውስጥ የፓርቲውን ፕሬዚዳንት ሃይሉ ሻውልን፤ ምክትል ሊቀመንበሯን ብርቱካን ሚደግሳን፤ ዋና ፀሃፊውን ሙሉነህ ኢዮኤልንና ለአዲስ አበባ ከንቲባነት ተመርጠው የነበሩትን ዶ/ር ብርሃኑ ነጋን ጨምሮ 12 አመራሮችን ባገር ክህደት፤በዘር ማጥፋት ሙከራ እንዲሁም በሌሎች ወንጀሎች ክስ በቁጥጥር ሥር አውለዋቸው ነበር፡፡

(ክፍል 1ሠን ይመልከቱ)

ኢህአዴግ ጋር ግንኙነት ያላቸውና ደጋፊዎቹ የፌዴሬሽን ምክርቤትን 108 መቀመጫዎች በሙሉ ተቆጣጥረዋቸው ነበር ። የዚህ ምክር ቤት አባላት የሚሾሙት በክልል መንግሥታትና በፌደራል መንግሥት ነው ። ለአባላቱ የኢህአዴግ አባል መሆን ጥቅም ነበረው፡ ኢህአዴግ ብዙ ድርጅቶችን በባለቤትነት ያንቀሳቅስ ስለነበረ ለደጋፊዎቹ ሥራ ይሰጥ ነበርና ።

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ብዙ ቦታ የነበረው ተቃዋሚ ፓርቲ የቀድሞውን የቅንጅት አባላት አካቶ በአዲስ መልክ የተቋቋመው የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ሲሆን 61 መቀመጫዎች ነበሩት ።

የተመዘገቡ የፖለቲካ ፓርቲዎች በክልሎች ቢሮዎች ለመክፈት የክልል መንግሥታት ፈቃድ ማግኘት ነበረባቸው ። እንደ ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ/ቅአዴፓ/፤ ሕብረትና ኦፌዴን ያሉ ፓርቲዎች ባመቱ ውስጥ የክልል መንግስታት ባለስልጣናት በአባሎቻቸው ላይ ያደርሱት የነበረው ማስፈራራትና ጥቃት ቀጥሎ እንደነበረ ተናግረው ነበር ። ተቃዋሚ ፓርቲዎችና ጋዜጦች እንደዘገቡት ግድያዎችን፤ድብደባዎችን፤እስሮችን፤የቤት ቃጠሎዎችንና የንብረት ውርሶችን ጨምሮ በመቶዎች የሚቆጠሩ ጉዳዮች ነበሩ ።

ባመቱ ውስጥ ባስልጣናት የተቃዋሚ አባላት ማዳበሪያ፣ ሌሎች የግብርና አገልግሎቶች የጤና ዕርዳታ ወይም ሌሎች በመንግሥት ሥር ያሉ ጥቅማጥቅሞች ማግኘት ከፈለጉ የተቃዋሚ አባልነታቸውን መተው እንዳለባቸው ይነግሯቸው እንደነበረ ሪፖርቶች ነበሩ ። ባለስልጣናት አብዛኛውን ጊዜ የተቃዋሚ ፖርቲዎችን ስብሰባዎች ይረብሹ ወይም ከሕግ ውጪ ያግዱ ነበር ። በ2003 መጨረሻና በ2004 መጀመሪያ ላይ ኢህአዴግ ስለዘጋው

የኮንሶ ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ ሕብረት /ኮህዲህ/ ቢሮና በአብዛኛው የኮህዲህ አባላት የሚገኙባቸውን የአባሮባና የጃርሶ ጉባኤዎች ወይም በኮሂዲህ አባላት ላይ ስለደረሱት እስራና ድበደባዎች ምንም አዲስ ለውጥ አልነበረም፡፡ በ2004 የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ፓርቲ አባል የነበሩትን በቀለ ታደሰን በድንጋይ ደብድበው ለነበሩት ግለሰቦች ላይ ወይም መጋቢት 2005 የዚሁ ፓርቲ የአንኮበር ወረዳ አደራጅ ኮሚቴ ልቀመንበር የነበሩት ዘመድኩን ገ/ኪዳን ቤት ላይ ቦንብ በወረወሩት ሰዎች ላይ መንግሥት ምንም ርምጃ አልወሰደም ነበር፡፡

ከ19ኙ የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባላት ውስጥ ሁለቱ ሴቶች ሲሆኑ በዛ ያሉት ሴቶች ከፍተኛ ቦታ ነበራቸው፡፡ 547 መቀመጫ ባሉት የሕዝብ ተወካይ ምክር ቤት ውስጥ 116ቱ ሴቶች ነበሩ፤ ይህ ባለፈው ፓርላማ ከነበሩት 14 ሴቶችና ባለ 113 መቀመጫ የፌደሬሽኑ ምክር ቤት ካሉት 21 ሴቶች የተሻለ ነበር:: ከ14ቱ የጠቅላይ ፍርድ ቤት አባላት ውስጥ ሦስቱ ሴቶች ነበሩ፡፡ በግንቦት 2005ቱ ብሔራዊ ምርጫ ወቅት ከታዘቢዎች ፣ የፓርቲ ሠራተኞች እንዲሁም በምርጫ ጣቢያ ከነበሩ የምርጫ ባለሥልጣናት ውስጥ ግማሽ ያህሉ ሴቶች ነበሩ፡፡

የመንግሥት ሙስናና ግልፅነት

የፍትሕ ሚኒስቴር ዋነኛ ተግባር ሙስናን መዋጋት ነው፡፡ የሕብረተሰቡ ጫና ፣ ባሕላዊ ህጎችና የሕግ ክልከላዎች ባንድነት ሙስናን በተወሰነ ደረጃ ቀንሰውት ነበር፡፡ ይሁን እንጂ የመንግሥት ባለሥልጣናት የፕራይቬታይዜሽን ሂደቱን ለራሳቸው ጥቅም ሲያውሉት ታይቷል፡፡ በዚህም ምክንያት የመንግሥትና የፓርቲ የንግድ ድርጅቶች፤ የመሬት ሊዝና ብድር ለማግኘት ከሌሎች የተሻለ እድል ይሰጣቸው ነበር ፡፡ መንግሥት ሜድሮክ ለተባለውና በጣም ትልክ የሆነው የውጭ ኢንቬስተር የሲሚንቶ ማስመጣት ፈቃድ መስጠቱ ለመንግሥት እንደሚያዳላ ታይቶ ነበር፡፡ ሕጉ ሕዝቡ የመንግሥት መረጃ ማግኘት መብት እንዳለው ቢደነግግም በተግባር ግን ይህ መብት የተገደበ ነበር፡፡

መንግሥት ሕጎቹና መመሪያዎቹ በስራ ላይ ከመዋላቸው በፊት በሀገሪቱ ነጋሪት ጋዜጣ ያሳትማል ፡፡ የማስታወቂያ ሚኒስቴር በመንግሥት ፣ በጋዜጦችና በሕዝቡ መሃከል ያለውን ግንኙነት የሚያመቻች ቢሆንም መንግሥት ግን በተደጋጋሚ ከግሉ ፕሬስ የሚቀርቡለትን ጥያቄዎች የመመልከት ፈቃደኛነት አልነበረውም፡፡ (ክፍል ሁለት ሀን ይመልከቱ)

ክፍል 4 በአለም አቀፍ ድርጅቶችና በመያዶች አሉ በሚባሉ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ ስለሚደረግ ማጣራት መንግሥት ያለው አመለካከት፤

በዛ ያሉ ያገር ውስጥና አለምአቀፍ የሰብዓዊ መብት ቡድኖች ባጠቃላይ በተወሰነ የመንግሥት ገደብ በሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ላይ ማጣራት በማድረግና ግኝቶቻቸውን በማሳተም ይንቀሳቀሳሉ ። ባጠቃላይ መንግሥት ባገር ውስጥ ሰብዓዊ መብት ቡድኖችና በጥቂት አለምአቀፍ ታዛቢዎች ላይ ጥርጣሬ አለው ።መያዶች ከውጪ ሊያስገቧቸው በሚፈልጓቸው የህትመት ሥራዎች ላይ የተጣሉትን ገደቦች ከማማረራቸውም በላይ የውጪ ጎብኚዎችን፤ ለማምጣት ተከልክለው እንደነበርም በምሬት መናገራቸውን ቀጥለው ነበር ። በሚያዝያ 2005 መንግሥት በዛ ያሉ በምርጫ ዙሪያ የሚሰሩ መያዶችን ተወካዮች ካገር አስወጥቶ ነበር በዓመቱ መጨረሻም እንዲመለሱ አልፈቀደላቸውም።

ከዋና ዋና ያገር ውስጥ ሰብዓዊ መብት ድርጅቶች መካከል ሁለቱ ኢሰመጉና የሕግ ባለሞያ ሴቶች ማህበር ነበሩ ። በተደጋጋሚ መንግሥት የኢሰመጉን ሪፖርቶች ሲያጣጥልና ኢሰመጉ የፖለቲካ ድርጅት ነው ሲል ቆይቷል። በታህሳስ 2005 ከኢሰመጉ ዋና ዋና መርማሪዎች ውስጥ ሁለቱ የነበሩት ቸርነት ታደሰ እና ያሬድ ሃይለማርያም የቅንጅትን መሪዎች ጨምሮ ከ111 ሌሎች ሰዎች ጋር ታስረው ለፍርድ ቀርበው ነበር ። /ክፍል 1 ሠን ይመልከቱ/

የሕግ ባለመያ ሴቶች ማህበር ዋነኛ ተግባሩ ሴቶችን በሕግ መወከል ነበረ። እነዚህና ሌሎች በሲቪክና ሰብዓዊ መብቶች ትምህርት፤ በሕግ እገዛና በፍርድ ሂደት ክትትል ላይ የተሰማሩ ብዙ ቡድኖች ነበሩ ። ይሁን እንጂ መንግሥት ለአገር ውስጥ የመያድ ማህበረሰብ አባላት በሰብዓዊ መብቶች ዙሪያ ምንም ዓይነት መረጃ ካለማካፈሉም በላይ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች መኖራቸውን እንኳን አምኖ አያውቅም ነበር ።

መንግሥት የሰብዓዊ መብቶች ሊግ የተባለውን ድርጅት ከአነግ ጋር ግንኙነት አለው በሚል መከታተሉን ቀጥሎ ነበር። የሊጉ ቢሮዎች እንደተዘጉ ቆይተዋል። መንግሥትም ድርጅቱ በ1997 ላቀረበው የምዝገባ ጥያቄ፤ ምንም እንኳን ፍርድ ቤት እንዲመዘገብ ቢፈርድለትም፤ ባመቱም መጨረሻ ምንም መልስ አልሰጠም ነበር ።

አልፎ አልፎ መንግሥት እንደ ተባበሩት መንግሥታትና አለም አቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴ ካሉ አለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ትብብር ያደርግ ነበር ። ይሁን እንጂ የአለም አቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴ ፌደራል እስር ቤቶችንና የፖለቲካ እስረኞችን እንዳሻው መጎብኘት አይችልም ነበር ።(ክፍል 1 ሐ ንና መ ን ይመልከቱ)

ሕጉ መንግሥት በአስፈፃሚው አካል ቅርንጫፍ ቢሮዎች በሚያጋጥሙ አስተዳዳራዊ ስህተቶች ምክንያት የተፈጠሩ ቅሬታዎችን ተቀብሎ የማጣራት ስልጣን የተሰጣቸውን የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽንንና የእንባ ጠባቂ ተቋምን እንዲያቋቁም ያዛል። ሁለቱም ተቋሚት ተቋቋመዋል፤ ነገር ግን ባመቱ መጨረሻ ሁለቱም ባግባቡ ሥራቸውን አልጀመሩም ነበር ።

የፍትሕ ሚኒስቴር ባገሪቱ ለሚገኙ ዳኞች፤ አቃቢያነ ሕግ፤ ፖሊሶችና የማህበረሰብ አባላት በሰብዓዊ መብቶች ላይ ያተኮረ የ3ዓመት የስልጠና ፕሮግራሙን ቀጥሎ ነበር። ነገር ግን ከምርጫ ጋር የተገናኙ ብጥብጦች ይህ ስልጠና ባግባቡ እና በተገቢው ጊዜ እንዳይካሄድ አስገድደውት ነበር ።

በ2003 መጨረሻና በ2004 መጀመሪያ ላይ በጋምቤላ ክልል ተከስቶ በነበረው የብሔረሰቦች ግጭት ምክንያት ተፈፀሙ የተባሉ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን በተመለከተ የፓርላማው ኮሚሽን ሪፖርት አቅርቦ ነበር ። (ክፍል 5ን ይመልከቱ) ሂዩማን ራይትስዎች በመጋቢት 2005 ሪፖርት እንዳደረገው ይኸው ኮሚሽን በጎሣ ግጭቱ ምክንያት የሞቱትን ሰዎች ቁጥር በእጅጉ አሳንሶት ነበር ።

ባመቱ ውስጥ ስድስት የጦር ሰራዊቱ አባላት በ2003ቱ የሰላማዊ ዜጎች ግድያ በመሳተፋቸው ተከሰው ነበር። ባመቱ መጨረሻም የፍርድ ሂደታቸው አንደቀጠለ ነበር።

በመስከረም ሁለት የአለም አቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴ ሰራተኞች በሶማሌ ክልል በተባበሩት የምዕራብ ሶማሌ ነፃ አውጪ ግንባር ታግተው ነበር ። ከ5 ቀናት በኋላ ምንም ጉዳት ሣይደርስባቸው ሁለቱም ተለቀዋል ።